ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
ንጉሠ ጽዮን፥ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ

እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር አድርሳ የምትኖረው ኢትዮጵያ፣
የመሲሓችን እናትና የእኛም እናት፣
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም
የንጉሦችና የንግሥቶች ንግሥት፡
እግዝእተብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።

---

መስከረም ፲፪ ቀን ፳፻፲፩ ዓ. ም.

## የኪዳናዊ ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ (የአኵስም ንቡረ-እድ) ወስመጥምቀቱ ኂሩተወልድ የሽኝት በዓል (በዓለ ማዕዶት) ዝክረ ነገር።

ልዑል እግዚአብሔር፡ ከዘመነ ማርቆስ፡ ወደዘመነ ሉቃስ አሸጋግሮ፡
የኢትዮጵያን የነጻነት ህልውና በዓላችንን የ፯ሺ፭፻፲፩ (የሰባት ሺህ አምስት መቶ ዐሥራ አንደ)ኛውን ዓመት፣
እንዲሁም፡
የአዳምና የሔዋንን ልደት፥
የቅዱሱ ኪዳን፡ መነሻ የኾነው ሥርዓተ ጋብቻም የተከሠተበትን ቀን ያካተተውን፡ የፍጥረትን መገኛ
፯ሺ፭፻፲፩ኛውን ዓመት በዓል፥
ደግሞም፡
የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን፡ የ፪ሺ፳፯ (የኹለት ሺህ ሃያሰባተ)ኛውን ዓመት
እና
የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ የ፪ሺ፲፩ (የኹለት ሺህ ዐሠራአንደ)ኛውን ዓመት፡
የትስብእት ልደታት በዓሎቻችንን ለማክበር ለበቃንበት፡ ለአዲሱ፡ የ፪ሺ፲፩ (፳፻፲፩)
(ኹለት ሺህ ዐሥራአንድ፥ ወይም፡ ሃያ መቶ ዐሥራአንድ፥ ወይም፡ ዕሥራ ምእት ወዐሠርተአሐዱ)
ዓመተ-ምሕረት፥ እንኳን፡ በያለንበት፡ በሰላም አደረሰን!

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የቅዱሱ ኪዳን ልጇና ኣገልጋይዋ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወደዚህ ዓለም በሥጋ በተወለደበት በ፹፪ ዓመቱ፡ መስከረም ፳ ቀን ፪ሺ፲ ዓ. ም. በዕለተ ሰንበት፡ ሕያዊት ነፍሱ ከክቡር ሥጋው በሰላማዊ እንቅልፍ ተለይታ፡ በይባቤ መላእክት፡ ወደ ፈጣሪዋ ተመልሳለች። ጥቅምት ፲፬ ቀን፡ በመኖሪያ ቤቱ የጸሎትና የምስጋና ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ፣ ክቡር ሥጋው ወደ እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተ-ክርስትያን ተሸኝቶ፡ የማሕሌትና ሽብሸባ ምስጋና ሌሊቱን ሲካኼድ ኣድሮ፡ በማግስቱ ጥቅምት ፲፭ ቀን፡ የቅዳሴ ሥርዓት ተካኺዶ፡ ከቀኑ በ፫ ሰዓት፡ ግብዓተ መሬቱ ተፈጽሟል።

ከኹሉ ኣስቀድመን፡ የኪዳናዊ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ዜና ዕረፍቱ ከተሰማበት፡ የሽኝቱ ቀን እስኪታወቅ ድረስ፡ ስሜታችሁን ለመግለጽ በመኖሪያ ቤታችን ደክማችሁ መጥታችሁ፡ ቤተሰቡን ሳታገኙ ኣዝናችሁ ለተመለሳችሁ ወዳጆችና ዘመዶች፥ ተከስቶ በነበረው ያልተጠበቀ ኹኔታ፡ በጊዜው ተቀብለን

ልናስተናግዳችሁ ባለመቻላችንና፡ በሽኙቱ ጊዜም ይቅርታ ባለመጠየቃችን፡ ከልብ ያዘንን መኾናችንን እያሳወቅን፥ አሁንም ይቅርታችሁን፡ በቃል ኪዳን አምላካችን በእግዚአብሔርና በእናታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ስንጠይቅ፡ እንደምትቅበሉት በመተማመን ነው። በአገር ውስጥና በመላው ዓለም ለሚገኙ የንቡረ-እድ ኤርምያስን ትምህርትና መልእክቶች ለሚከታተሉ ኹሉ፡ እንዲሁም መረጃውን ለማግኘት ሲጠባበቁ ለነበሩ፥ ይህ ያልታሰበ ኹኔታ የተፈጠረበትን ትክክለኛ ምክንያት ማሳወቅ ኣግባብ መኾኑን ብንገነዘብም፥ ምቹ ኹኔታ ባለመፈጠሩ መክንያት ሳንገልጽ ቆይተናል። ጊዜው የተራዘመ ቢኾንም፡ በቤተሰቡ የደረሰውና ያጋጠመው ትክክለኛ ሂደት፡ በዝርዝር መገለጹ ተገቢ ስለኾነና፡ ይህም ኣጋጣሚ ትክክለኛና መታለፍ የሌለበት በመኾኑ፥ ከዚህ ቀጥሎ ዝርዝሩን እንደሚከተለው ኣቅርበነዋል።

በመጀመሪያ፡ ኪዳናዊት ባለቤቱን ወይዘሮ ራሔል ዘካርያስን እና ኪዳናዊያንና ኪዳናዊያት ልጆቹን ከያሉበት፣ ከውጭ ኣገራት ተሰባስበው ወደ መኖሪያ ቤታቸው እስኪመጡ ድረስ መጠበቁ ኣስፈላጊ ነበር። በመቀጠል ደግሞ፡ የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ፡ ንቡረእድ ኤርምያስ ከበደ፡ ዘወትር ሳያስታጉል በሚፈጽመውና ሌላውም እንዲፈጽመው በሚመክረው ሥርዓት መከናወን ነበረበት፤ ይኸውም፡ የሥነ-ፍጥረት ባለቤት የኾኑት "የይሁዳው ኣንበሳ ድል ነሣ!" የተባለው እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ እና "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ታደርሳለች!" የተባለችው እግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና መደብ ላይ ተወክለው የሚታዩበትን የእግዚአብሔር መንግሥት መለያ ሰንደቅ ዓላማ፡ በከፍታና በይፋ በማውለብለብ የሚፈጸመው፣ እግዚአብሔር የግዙፉም የረቂቁም ዓለም ፈጣሪ፣ ኣስገኚ፣ መጋቢ እና ኣስተዳዳሪ መኾኑን ዕውቅና የሚሰጠው ሥርዓት ነው። ይህንን ሥርዓትም መፈጸም የተፈለገው፡ ኣያቱ ቄሰገበዝ ወልደኢየሱስ ኣምኃ-ሥላሴ ወልደኢየሱስ በመሠረቱትና በክህነት ባገለገሉበት፣ ኣባቱ መምሬ ከበደ በቅስና ክህነት ባገለገሉበት፣ እራሱ ኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ፡ በእውነተኛነት፣ በቀናነት፣ በታታሪነት፣ በቆራጥነት እና በጀግንነት ከዲቁና፥ ቅስና፥ እስከ እልቅና ባገለገለበት በመካነ-ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ የቤተሰብ ማረፊያ ውስጥ ነበረ።

ሽኙቱን በቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ለማስፈጸም፡ ውጭ ኣገር የነበሩ ባለቤቱን ወይዘሮ ራሔልና ልጆቹን በመጠባበቅ ላይ እያለን፥ የደብሩ ኣለቃ መላከጸሓይ በቀለ ተሰማ፡ የቀብር ሥርዓቱን በቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ለማድረግ ተቃውሞ ያጋጠማቸው ስለኾነ፡ ቤተሰቡ ለጠቅላይ ቤተ ከህነት ኣመልክቶ፡ በጽሑፍ ፈቃድ እንድናመጣ እንደሚያስፈልግ፡ ቀደም ብሎ በቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን በዲያቆንነት ያገለግል የነበረ፡ ፍቅረ ኃይለሥላሴ በሚባል በኩል፡ በመልእክት ተገለጸልን። ቤተሰቡም፡ ኣያቱ ቄሰገበዝ ወልደኢየሱስ ኣምኃ-ሥላሴ ወልደኢየሱስ በመሠረቱትና በክህነት ባገለገሉበት፣ ኣባቱ መምሬ ከበደ በቅስና ክህነት ባገለገሉበት፣ እራሱ ቄስ ኤርምያስ ከበደ፡ ከዲቁና፥ ቅስና፥ እስከ እልቅና ባገለገለበት በመካነ-ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ የቤተሰብ ማረፊያ ውስጥ፡ ሥጋውን ለማሳረፍ፡ ፈቃድ መጠየቅ ተገቢ እንዳልኾነና እንደማናምንበት ገልጸን፣ ምላሻቸውን ስንጠባበቅ መቆየት ግድ ኾነ። ኾኖም፡ ይህ ኹኔታ የመንፈስ ውጊያው የቀጠለበት መገለጫ መኾኑን ስለተገነዘብን፡ የመለኮትን ፈቃድ በሱባዔ መጠየቅ እንዳለብን ተረዳን።

በዚህ ጊዜም መፍትሔ ሊኾኑ ይችላሉ ያልናቸውን ብዙ ኣሳቦች ያወጣን ያወረድን ሲኾን፡ ከነዚያም መካከል የሚከተሉት ዓበይት የሚባሉት ናቸው፡-

- በሌሎች የቤተ ክርስቲያኗ ቅጽሮች ውስጥ ለማሳረፍ፣ ለምሳሌ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ፣ በደብረሊባኖስ፣ በቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ፣ በአክሱም ጽዮን እና በመሳሰሉት ታስቦ ነበር። ነገር ግን በእነዚህ ቦታዎችም ቢኾን፡ የኢትዮጵያ እግዚአብሔር መንግሥት ሰንደቅ ዓላማን በይፋ እያውለበለቡ ማንኛውንም ዓይነት ሥርዓት መፈጸምን፡ በጊዜው በጥብቅ ኹኔታ ይተገበር የነበረው የኣገሪቱ የሰንደቅ ዓላማ ኣዋጅ የሚፈቅደው ጉዳይ ኣልነበረም።

• ግዙፉም ኾነ ረቂቁ ዓለም ኹሉ የእግዚአብሔር ስለኾነ፡ ሰንደቅ ዓላማው ደግሞ፡ ለዚያ መንግሥቱ ዕውቅና የሚሰጥ እስከኾነ ድረስ፡ ለምን የቀብር ሥነ-ሥርዓቱን ይህንን ሰንደቅ ዓላማ ከማይከለክሉ አገራት መካከል በአንዱ አንፈጽመውም በማለት፡ ወደፊት አጽሙ በኢትዮጵያ በተገቢው ቦታና ሥርዓት እስኪፈጸም፡ የጋሽዬን ክቡር ሥጋውን ወደ አሜሪካ ሜሪላንድ ወስዶ ለጊዜው ለማሳረፍ፡ ታስቦ ነበር። ነገር ግን፡ ይህንን ማድረጉ ደግሞ፡ ለአገረ ሙላዳችን፣ ኢትዮጵያ የሚሰጠውን አሉታዊ ገጽታ በማሰብ ወዲያውኑ እንዲቀር ኾኗል።

ከዚያም እነዚህንና ሌሎቹንም አሳቦቻችንን በማሰባሰብ፡ በጥቅምት ፫ ቀን ፳፻፲ ዓ. ም. ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ በሚያምንበት፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት፥ የቅዱሱ ኪዳን ዓርማ ያለበትን ሰንደቅ ዓላማ አልብሰን፡ የሽኝቱ ሥርዓት በሕጋዊ መንገድ እንዲፈጸም በማመልከት፡ በቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን የቤተሰብ ማረፊያ ቤት ሥጋው እንዲያርፍ ፈቃዳችን እንደኾነ፡ ለጠቅላይ ምሉክ ጽሕፈት ቤትና ለኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ/ መንበረ ፓትርያርክ ጽሕፈት ቤት፣ ደብዳቤ አስገባን። ግልባጭ፡ ለርዕሰ ብሔሩ፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤና፣ ለመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ደብር አስተዳደር ጽሕፈት ቤት እንዲደርስም አድርገናል።

መልሱን በመጠባበቅ ላይ እያለን፡ ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ምሉክ የተወከሉ ስልክ በመደወል፡ ደብዳቤው እንደደረሳቸውና፡ ጉዳዩን በተጨማሪ ለመረዳት ሊያነጋግሩን እንደሚፈልጉ ገልጸውልን፡ ኹኔታውን ከቤተሰቡ አባል ካጣሩና ከተረዱ በኋላ፥ በጥያቄያችን መሠረት፡ ጽሕፈት ቤቱ ሥርዓቱን ብንፈጽም እንደማይቃወም፡ ነገር ግን፡ ሌላ ዓላማ ያላቸው ሰዎች፡ የቀብር ሥነ-ሥርዓቱን የሚከታተሉ መስለው፡ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የሚውለበለበውን ሰንደቅ ዓላማ በተንቀሳቃሽ ስልክ አንስተው፡ በተለያዩ የመገናኛ ዓውታሮች ለተመልካች ማስተላለፋቸው እንደማይቀርና፡ ከዚያ የተነሣም፡ አቃቤ ሕግ የሰንደቅ ዓላማ ሕጉን በመፃረር ተጠያቂ ሊያደርገን እንደሚችል የገለጹልን ሲኾን፡ በተጨማሪም፡ የማረፊያ ቦታውን በሚመለከት፡ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጋር እንድንጨርስ ተማጽነው፣ አስፈላጊ ከኾነም ጥበቃ እንደሚደረግልን ቃል ገብተው፥ በታሪክ የብዙ ቅዱሳን አጽም በየጫካውና በየበረሃው ወድቆ እንደሚቀር፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ግን በቤተሰቡ እጅ መኾኑ ዕድለኛ እንደኾነ፡ ወንድማዊ የማጽናኛ ምክርም ለግሰውን፡ በአክብሮትና በታላቅ ትሕትና አነጋግረውናል።

ለአሥር ቀናት ከጠቅላይ ቤተክህነት ጽሕፈት ቤት መልስ ከተጠባበቅን በኋላ፥ ጉዳዩን በቅርብ በምትከታተል የቤተሰቡ አባል፡ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤትና አዲስ አበባ አገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት ድረስ በመገኘት ባደረገችው ክትትል፡ ጉዳዩ እንዳልቀረበና ምንም ዓይነት እርምጃ እንዳልተወሰደ፣ ተቃውሞውንም ያቀረቡት እነማን እንደኾኑ እንዳልተረጋገጠ ለማወቅ ችለናል። በሃያ ኹለተኛው ቀን፡ ጉዳዩ ወደፊት እንደሚጣራ አረጋግጠው፥ በየትኛው ደብር ሥርዓቱ እንዲከናወን እንደምንፈልግ ከአገረ ስብከቱ ተጠየቅን። እኛም፡ እግዚአብሔርና ቅድስት ድንግል ማርያም በፈቀዱት፡ በእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተ ክርስቲያን፡ እንዲኾን የምንፈልግ መኾናችንን አሳወቅን። በነሱ በኩልም ማንኛውም ትብብር እንደሚደረግልን ተገለጸልን። በዚህ መሠረት፡ ጥቅምት ፲፩ ቀን፡ ለሃያ አምስት ቀናት፡ ቀዝቃዛ ቤት ከቆየበት፡ ከአዲስ ህይወት የሕክምና ማዕከል አውጥተን፡ በመኖሪያ ቤቱ ምስጋና ለማቅረብ ጥቂት ካቆየነው በኋላ፥ ምሽቱን በቤተሰቡ ታጅቦ፡ ወደ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎተ ፍትሐት ተወሰደ፤ እዚያም በደብሩ ካህናት የማኅሌት ምስጋናና ሽብሸባ ሌሊቱን ሲካኼድ አደረ።

ይህንን የማደናቀፍ ሴራ የወጠኑት የዲያቢሎስ ጭፍሮች፡ ሽኝቱ ከመፈጸሙ በፊት፡ ክቡር ሥጋው ቤተ-መቅደስ ውስጥ ኾኖ፡ የቅዳሴ ሥርዓት እየተካሔደ፡ ሥርዓቱን የሚያስፈጽሙትን የቤተሰቡን አባላትና በጊዜው የነበሩትን የደብሩን ጸሓፊ እያስፈራሩ፡ ክቡር ሥጋውን ከቤተ-መቅደስ እንዲያወጡ ትእዛዝ በመስጠት፡ ሁከትና ረብሻ ለመፍጠር ብዙ ሞክረው፥ ተጠባባቂ ጸሓፊው ባለባቸው ኃላፊነት፡ ሊያስከትል የሚችለውንም ችግር ሳይፈሩ ቆርጠው በመጋፈጣቸው፡ ሳይሳካላቸው ቀርቷል። የአገረ ስብከቱም ወኪል፡

ሁከቱን የሚፈጥሩት ግለሰቦች፡ በቂ ማስረጃ እስካላቀረቡ ድረስ፡ ምንም ነገር ቢመጣ እንደሚወጡት ጳሓፊውን እያበረታቱ፡ ኹለቱም ትልቅ መስዋዕትነትን ከፍለው፣ ካህናቱም ከሌሊት ጀምረው በታላቅ የበዓል ሥርዓት አድምቀው፡ ሸኝቱ በክብር ሊፈጸም በቅቷል። የሽኝቱ ሥርዓት ከተፈጸመ፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ፡ ቤተሰቡንና ተጠባባቂ ጳሓፊውን ስልክ እየደወሉ ሲያውኩ የነበሩ ሦስት ግለሰቦች፡ በሕዝብ ደህንነት ተይዘው እየተጠየቁ መኾኑ ቤተሰቡ እንዲያውቀው ተደርጓል።

> "በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ኹኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ኹሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፡ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር፡ በሰማያዊም ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ኹሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ኹሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ምሥራችም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በኹሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ኹሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር፡ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፡ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።" (ኤፌሶን ምዕ. ፮ ቁ. ፲-፲፰)

ሽኝቱ በሰላም ከተጠናቀቀ ከጥቂት ቀናት በኋላ፡ ከአዲስ አበባ አገረስብከት ጽሕፈት ቤት የተወከሉ፡ በመኖሪያ ቤታችን መጥተው፡ ንቡረ እድ ቄስ ኤርምያስ ከበደ፡ የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት የሚያካኼድበትን፥ ሰንደቅ ዓላማውንም ጨምሮ፡ ጠቅላላ ጉብኝት ከማድረጋቸውም በተጨማሪ፣ ያለውን ኹኔታ አጣርተው በዝርዝር ከተረዱ በኋላ፥ በተፈጠረው ኹሉ ማዘናቸውን በእንባ ጭምር ገልጸው፣ ቤተሰቡም እንዳንቀየም አጽናንተው፣ ምክራቸውንም ለግሰው፡ ጸሎትና ቡራኬ ሰጥተው ተሸኝተዋል።

ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት መልእክተኛ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ (ኂሩተወልድ)፡ አገልግሎቱን ከጀመረበት ከወጣትነት ዕድሜው ጀምሮ፡ የእግዚአብሔርን እውነት በመመስከርና ምሥራቹን በማብሠር፣ እንዲሁም፡ *"የቤትህ ቅናት በልታኛለችና"* የሚለው የዳዊት መዝሙር፡ በእርሱም ውስጥ የተቃጠለ ቅዱስ መንፈስ ዕረፍት ስለማይሰጠው፥ ኾን ተብሎ ለዘመናት ተድበስብሶና ሕዝቡ ተተብትቦበት የኖረውን የዲያብሎስን ሓሰት፡ በድፍረት አጋልጦና ዕቅዱን አፈራርሶ፥ ምንም ፈተና ሳይበግረው፡ እስከመጨረሻው ተጋድሎ፥ ቃልኪዳን የገባለት ተልዕኮውን በመፈጸሙ፥ ሕያዊት ነፍሱ በሚገባት የቅዱሳን ቦታ የልጅነት፣ የክህነት፣ የንግሥናና የክብርን አክሊል ተቀዳጅታ፡ በደስታና በሓሴት፡ ዘለዓለማዊ የመንግሥተ ሰማያት ሕይወቱን ቀጥሏል። ይህንን ያወቀው ዲያብሎስ፡ በቅናት፥ በንዴትና በቀቢጸ ተስፋ፡ በቀረው ጥቂት ጊዜ፡ በሚያደርገው ሩጫና የመጨረሻ መፍጨርጨር፥ ቤተሰቡንና ወዳጆቹን ለማስበርገግና ለማስደንገጥ፣ ለማዳከምና ለመፈተን፥ ሸብር በመፍጠር፥ *ባለቤቱ ኢየሱስ መሢህ "ነቢይ በአገሩ አይከበርም"* ብሎ እንደተናገረው፡ የሰይጣን ግብረአበሮችና መሣሪያዎች በኾኑ፡ በቅርብ በሚታወቁ ሰዎች፡ ክቡር ሥጋው የትም እንዲወድቅና ማሳረፊያ ለማሳጣት የተቀነባበረው ሙከራ ከሽፎ፥ በታማኝነት ያገለገላቸው የቃል ኪዳን አምላኩ ኢየሱስ መሢህና ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ ኹሉንም ወደበጎ ለውጠው፡ በድል አድራጊነት ሽኝቱን በተገቢው የተቀደሰ ቦታ፡ በመልካም እንዲከናወን አድርገውለታል።

በተጨማሪም፡ በመንፈስ የማደግ ብሎም እግዚአብሔርን የመምሠልና የመኾን ብቃት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥበብና ዕውቀት፥ ኃይልና ሥልጣን የተሰጠው የሰው ልጅ፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሠራውን ሥርዓት በጥልቅ ባለመረዳት ብቻ ሳይኾን፡ ኪዳናዊ ኤርምያስን ለራሳቸው ምድራዊ ሥልጣንና ጥቅም መሣሪያ እንዲኾን ይፈልጉ የነበሩ፥ የተነበዩት ትንቢት ተፈጻሚ ያልኾነላቸው፡ አገልግሎቱን አልፎ አልፎ የሚነቅፉና የሚያጥላሉ ጥቂት ግለሰቦች፥ ምናልባትም ያልተረዱት፡ እነሱና እኛ ጫማ አድርገን፡ ልብስ ለብሰን፡ በሰላም የምንወጣውና የምንገባው፥ እሱና እንደሱ ያሉ በባዶ እግራቸውና ራቁታቸውን ሸማ አጣፍተው በመኼዳቸው

እንደኾነ ያልተረዱ፣ እንዲሁም፡ በጀሯቸው የሚያንሾካሹካቸውን መንፈስ በጥልቅ ባለመመርመር ሲሰናከሉ ይታያሉ። ለነዚህ ሰዎች የምንለው፡ እውነት አንዲት ናት፥ እርሷም የእግዚአብሔር እውነት ናት፤ የመንፈስ ቅዱስ ትንቢትም ትክክለኛ ናት፡ አትለዋወጥም፤ ስለዚህ መንፈስን መርምሩ እንላለን። ኪዳናዊ ኤርምያስ ከአርባ ዓመት በላይ፡ በረዶና ውርጭ ሳይበግረው፡ በባዶ እግሩና ሸማ አጣፍቶ፡ በተለያየ የዓለም ክፍል በመንፈስ ጽናት እየተዘዋወረ የክህነት አገልግሎት ሲሰጥ፡ የጠፉ ወደንስሓ እንዲመለሱ ሲያስጠነቅቅና የቅዱሱን ኪዳን መልእክት ሲያስተላልፍ የነበረ ከመኾኑም በላይ፥ እንደ ሰላማችን ካህናችንና ንጉሣችን ኢየሱስ መሲሕ ቃል፡ በመጨረሻው ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥትን ለዓለም የሰበከ፥ ያስተጋባና የንስሓ ደወልን እየደወለ፡ የሰው ልጅ ከተኛበት እንዲነቃ ያለማቋረጥ እንደመሪው በኅብረተሰቡ መካከል እየተመላለሰ የእግዚአብሔርን እውነት ያለማቋረጥና ያለመታከት የተናገረ፥ የምሥራቹንም የሰበከ፥ የፈጣሪያችን የኢየሱስ መሢህና የእናታችንና የንግሥታችን እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ወታደር መኾኑን፡ እኛ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ቤተሰቦቹ ሕያው ምስክሮቹ ነን።

የቅዱሱ ኪዳን አገልግሎቱ፡ ጽናቱና ትዕግሥቱ እንደተፈተነና እምነቱም እንደወርቅ እንደነጠረ ኹሉ፥ የንቡረእድ ኤርምያስን አርአያነቱን በመከተል፡ እኛም የቅዱሱ ኪዳን የክህነት ባልደረቦቹና ቤተሰቦቹ፡ የደረሰውን ኹሉ በጸጋ በመቀበል፡ ለተደረገልን እና በኾነው ኹሉ፡ ለአባታችን እግዚአብሔርና ለእናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ክብርና ምስጋና ኹልጊዜ ማቅረባችንን አናቋርጥም።

> “እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ፡ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፤ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና፡ የሚያስጨንቃችሁን ኹሉ በእርሱ ላይ ጣሉት። በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባለጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉ ወንድሞቻችሁና እኅቶቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ፡ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት። በመሢህ ኢየሱስ ወደዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ኹሉ አምላክ፡ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል፡ ያጸናችሁማል፡ ያበረታችሁማል። ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን አሜን።” (፩ኛ ጴጥሮስ ምዕ. ፭፣ ቁ. ፮-፲፩)

ይህንን ታሪካዊ ሂደት መሠረት በማድረግ፡ በዘለዓለማዊቷ ሰንበት፡ እሁድ፡ መስከረም ፳ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ. ም. በዓለ ማዕዶቱን የምናከብርበት ዕለት በመኾኑ፥ ከሠላሳ አምስት ዓመታት በላይ በጸሎት፣ በምህላ፣ በሱባዔና በምስጋና፡ የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥትን መልእክት ሲያስተላልፍበት፣ የቅዱስ ኪዳን ሥርዓቱንም ሲፈጽምና ሲያስፈጽምበት ባሳለፈባት፡ የመኖሪያ ቦታው፡ በቋሚነት በየዓመቱ መታሰቢያውን ለማዘከር፡ አገልግሎቱንና መልእክቶቹንም ለሕዝብ ለማቅረብ፡ ከመስከረም ፳ ቀን ጀምሮ፡ ከተለመደው የመልከ ጼዴቅ የጠበል ጠዲቅ ሥርዓታችን ጋር፡ ለሦስት ቀናት ክፍት ኾኖ የሚቆይ ዓውደ-ርዕይ አዘጋጅተናል። ስለዚህ፡ የንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ የቅዱሱ ኪዳን ቤተሰቦች፣ ወዳጆችና ዘመዶች ኹሉ፡ የተዘጋጀውን የመታሰቢያ ዓውደ ርዕይ ተካፋዮች እንድትኾኑ፡ በትኅትናና በአክብሮት፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ ስም ተጋብዛችኋል።

የጌኑተወልድ በረከቱ ይደርብን!
የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ልጆችና አገልጋዮች
ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ቤተሰቦቹ